# ኢትዮጵያ

# የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ

የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን

ጥር 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## መግቢያ

የሽግግር ፍትሕ ሂደት በተለያዩ ደረጃዎች የሚከወኑ በርካታ፣ ውስብስብ እና እርስ በእርሳቸው ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን የሚጠይቅ በመሆኑ ለሂደቱ ውጤታማነት እያንዳዱ የሽግግር ፍትሕ ተግባር - ጊዜውንና የቅደም ተከተል ደረጃውን ጠብቆ በትኩረትና ጥንቃቄ ሊፈፀም ይገባዋል።

የሽግግር ፍትሕ ሂደት ሶስት ዋና ዋና የሂደት ደረጃዎችን የሚያካትት ሲሆን እነዚህም የሂደት ደረጃዎች የቅድመ-ሽግግር፣ የሽግግር እና የድህረ-ሽግግር ደረጃዎች ናቸው። እያንዳንዱ የሽግግር ሂደት ደረጃ በስሩ በርካታ ተግባራትን ያካትታል። የቅድመ-ሽግግር ሂደት ከሚካትታቸው ተግባራት መካከል የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሥራ አንዱና ዋነኛ ተግባር ነው። የሽግግር ፍትሕ ተግባራትን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በትክክል ለመተግበር እና የህዝብን ተሳትፎና አመኔታ ያተረፈ የሽግግር ፍትሕ ለማካሄድ እንዲቻል የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት - በጥናት ላይ የተመሰረተ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መቅረጽና መተግበር ወሳኝ ጉዳይ ነው።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የመቅረጽ ሥራ ከመሰራቱ በፊት በሽግግር ፍትሕ አስፈላጊነት ዙሪያ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትሕ በማካሔድ አስፈላጊነትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ ስለነበር በዘርፉ እውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የዳሰሳ ጥናት እንዲሰራ ተደርጓል። በዳሰሳ ጥናቱ ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትሕን መተግበር አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህን የጥናት ውጤት ተከትሎም መንግስት ለፖሊሲው ዝግጅት እና ትግበራ ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ጀምሯል። ፡

የፍትሕ ሚኒስቴር በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(1)(2) እንዲሁም የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(2) እና 40(1) መሰረት በሕግ ጉዳይ የፌዴራል መንግስቱ ዋና አማካሪና ተወካይ፤ እንዲሁም የፌዴራል ሕጎችንና ፖሊሲዎችን የማመንጨት ስልጣን ተሰጥቶታል። በመሆኑም የፌዴራል መንግስቱን ወክሎ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የማዘጋጀት ኃላፊነቱን በመውሰድ ልዩ ሙያ ያላቸው እና ገለልተኛ የሆኑ የባለሙያዎች ቡድን እንዲደራጅ በማድረግ የተለያዩ ስራዎች እንዲሰሩ አድርጓል።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የህዝብን ተሳትፎ እና እውቅና የሚሹ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ይጠይቃል። የቅድመ-ፖሊሲ ዝግጅት፣ የፖሊሲ ዝግጅት እና የድህረ-ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶችና ተግባራት የመንግስትን የአሰራር ግልጽነት፣ የህዝብን ተሳትፎ እና የፖሊሲ ዝግጅት ሥራውን ውጤታማነት በሚያረጋግጡ መልኩ እንዲመሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንፃር የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሞያዎች ቡድን በቅድመ-ፖሊሲ ዝግጅት፣ በፖሊሲ ዝግጅት እና በድህረ-ፖሊሲ ዝግጅቶች ሂደት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለህዝብ ይፋ የሚያደርግበት፤ እንዲሁም ስለሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ዝግጅት እና አሰራር በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን መድረኮች የሚያስረዳበት ስትራቴጂ (ስልት) መንደፍ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ጉዳዮች</u>

1. **ትርጓሜ**
    1) "ባለሙያ" ማለት የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች የስራ ቡድን አባል ሆኖ የተመደበ ባለሙያ ነው።
    2) "የስራ ቡድን" ማለት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንዲያዘጋጅ በፍትሕ ሚኒስቴር የተቋቋመው የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ስብስብ ነው።

3) "ተቋም" ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ነው።

4) "ከፍተኛ አመራር" ማለት የተቋሙ ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴዔታ ነው።

5) "ሚዲያ" ማለት የውጭ አገር ወይም በህግ አግባብ ፈቃድ ተሰጥቶት በአገር ውስጥ የሚሰራ የህትመት፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የማህበራዊ ሚዲያ ወይም ማናቸውም ዓይነት መገናኛ ብዙሃን ነው።

6) "የስራ ክፍል" ማለት የተቋሙ የህግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ጀነራል ነው።

7) "መረጃ" ማለት ስለ ሽግግር ፍትህ፣ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች፣ የፖሊሲ ዓላማ፣ አስፈላጊነት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሚዲያን እና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ለህዝብ ወይም ሌላ ማኛኛውም አካል በተቋሙ አመራር ወይም የባለሙያዎች ቡድን አባላት የሚሰጥ መረጃ ነው።

8) በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

## 2. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ (ከዚህ በኋላ ስትራቴጂ ተብሎ የሚጠራ) የስራ ቡድኑ አባላት ከሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ዝግጅት እና ሂደት ጋር በተያያዘ በከፍተኛ አመራሩ ወይም የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት ለሚዲያ ወይም ለሌላ ማንኛውም አካል መረጃ በሚሰጥ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 3. ዓላማ

የስትራቴጂው ዋና ዓላማ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ስራው ለህዝብ እና ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የሚሆንበትን ስርዐት በመዘርጋት - የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅቱ ሂደት እና ተግባራት ለህዝብ እና ለሚመለከታቸው አካላት ግልጽ ማድረግ፣ መረጃ መስጠት እና ህዝቡ የሚጠበቅበትን ተሳትፎ በአግባቡ እንዲወጣ ማድረግ የሚቻልበትን እድል መፍጠር ነው።

## 4. መርሆዎች

ስትራቴጂው በግልጽነት፡ ተጠያቂነት፡ አሳታፊነት፡ ታማኝነት፡ ሚስጥር መጠበቅ፡ አካታችነት፡ ፍትሐዊነት፡ ለሕግ እና ለሞያ ሥነ-ምግባር ተገዥ መሆን፡ እና የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች እና ተግባራት የኮሙኒኬሽን አቅጣጫዎች</u>

## 5. ለሕዝብ ስለሚደርስ መረጃ

1) ስለሽግግር ፍትህ ምንነት እና አስፈላጊነት፣ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ ስለሚደረግ የህዝብ ምክክር፣ ስለአስፈላጊነቱ፣ የፖሊሲው ዝግጅት፣ ስለፖሊሲው ዓላማ እና አስፈላጊነት፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሥራው ስለሚመራበት ሁኔታ፡ ከባለሙያዎች እና ከህዝብ ውይይቶች የሚገኙ ግብዓቶች በፖሊሲው ስለሚካተቱበት አካሄድ፡ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ - በከፍተኛ አመራሩ ወይም በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት - አስፈላጊው መረጃ ወቅቱን ጠብቆ ለህዝብ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ይደረጋል።

2) መረጃው ለህዝብ እንዲደርስ የሚደረገው በሚዲያ እና/ወይም በሌላ ማንኛውም ተመራጭ የመገናኛ ዘዴ ይሆናል።

3) በሀገርና በህዝብ ሰላም፣ ጥቅም እና አንድነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ከሚከተሉት ወይም መሰል ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት (ተግባር) ለህዝብ ወይም ለሚዲያ አካላት ግልጽ ላይደረግ ይችላል፦

- እንዲገለጽ የተፈለገው ወይም የተጠየቀው መረጃ እንዳይገለጽ በሕግ ክልከላ የተጣለበት ወይም መረጃው ቢገለጽ በሀገር ወይም በህዝብ ላይ ወይም በተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ላይ ቅሬታን የሚፈጥር ወይም ወንጀልን የሚያስከትል ወይም በሰዎች ወይም በመንግስት አካላት መካከል ያልተገባ ቅራኔና መቃቃርን የሚፈጥር ሆኖ ሲገኝ፤
- የሂደቱ ወይም የተግባሩ መገለጽ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሥራውን ያስተጓጉላል ተብሎ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አዘጋጅ ከፍተኛ የባለሞያዎች ቡድን ሲታመን፤
- ሂደቱ ወይም ተግባሩ ልዩ የሞያ ሚስጥርን የሚጠይቅ ወይም የሂደቱ ወይም የተግባሩ መገለጽ ለህዝብ የማይጠቅም ወይም አስፈላጊነት የሌለው ሲሆን፤ ወይም
- ሌሎች ለህዝብ ጥቅም ሲባል መረጃ ለህዝብ ወይም ለሌላ ማንኛውም አካል መረጃ እንዳይወጣ በከፍተኛ አመራሩ የሚለዩ ጉዳዮች።

6. **መረጃ ስለሚሰጡ ሰዎች እና መረጃው ስለሚሰጥበት ሁኔታ**

1) መረጃ ለሚዲያ ወይም ለሌላ ማንኛውም አካል የሚሰጠው በሚከተለው አካላት ብቻ ይሆናል፤

ሀ) በተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች፣

ለ) ተለይተው በተሰየሙ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ አባላት፡

ሐ) ስልጣን ባለው ሌላ የመንግስት አካል፣

መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ተለይተው የተመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ በተቋሙ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፣

2) በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር በተቋሙ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት አማካኝነት መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ በፅሁፍ፣ በድምጽ፣ በቪዲዮ ወይም ሌላ አማራጭ የተሰጠን መረጃ በተቋሙ ድረ-ገጽ፣ የፌስ ቡክ ገጽ፡ በሌላ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም መደበኛ ሚዲያ አማራጭ መረጃውን በመላክ ብቻ ነው።

3) በተፈቀዱ ሁኔታዎች ባለሙያዎች ለማንኛውም አካል መረጃ የሚሰጡት በሚከተሉት መንገዶች ነው፡--

ሀ) በተቋሙ ድረ-ገጽ ወይም በሌለ የተቋሙ ማህበራዊ ሚዲያ፣

ለ) ሚዲያ ላይ ገጽ ለገጽ በመቅረብ፣

ሐ) ለሚዲያ መረጃን በጽሁፍ፡ በድምጽ ወይም በምስል በመላክ፣ ወይም ዶክመንታሪዎችን በማዘጋጀት፡

መ) በሌላ እውቅና በተሰጠው ዘዴ።

4) ባለሙያዎች ከሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ጋር በተያያዘ እርስበእርስ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ደረጃ ከሌላ ማንኛውም አካል ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ ለስራ ቡድኑ በተዘጋጀው ኢሜል ወይም እውቅና በሚሰጠው ሌላ መገናኛ ዘዴ ብቻ ይሆናል።

7. **የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት መረጃ ሊሰጣቸው የሚችሉ አካላት**

ለህዝብ መድረስ የሚገባውና ሊገለጽ የሚችል ማንኛውም መረጃ በራሱ በባለሙያዎች ቡድኑ አመቻችነት በሚዘጋጅ የኮሙኒኬሽን መድረክ ወይም በስትራቴጂው የተቀመጡ የጥያቄ ማቅረቢያ መንገዶችን ተከትሎ ጥያቄ ላቀረበ የመገናኛ ብዙሃን እና ህጋዊ ፍቃድ ላለው ማንኛውም አካል ሊሰጥ ይችላል። በዋናነትም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- የመንግስት/ግል የቴሌቪዥን ድርጅቶች፣
- የመንግስት/ግል የሬዲዮ ጣቢያዎች/ድርጅቶች፣
- የመንግስት/ግል የሕትመት ሚዲያዎች፣
- ህጋዊ ፈቃድ ያላቸውና ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲዘግቡ ለተፈቀደላቸው የውጭ መገናኛ ብዙሃን፣
- ለውጭ አገር ሚዲያዎች፣
- ጥናታዊ ጽሁፍ የሚሰሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች፣ እና
- ሌሎች በከፍተኛ አመራሩ አቅጣጫ መረጃ እንዲሰጣቸው የተለዩ አካላት።

## 8. መረጃ የሚሰጥበት መንገድ

በራስ ተነሳሽነት እና በመገናኛ ብዙሃን ጥያቄ መነሻነት ከሚሰጠው መረጃ በተጨማሪ - ከመንግስት እና ከግል የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችን ወይም የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም፡ እንዲሁም የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የማህበራዊ ሚዲያ አውታር (ፌስ ቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ድህረ-ገጽ፣ ኢሜይል፣ ቴሌግራም፣ ትዊተር፣ ዋትስአፕ፣ ኢንስታግራም፣) በመጠቀም መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ሥራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል።

## 9. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት

1) ለሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አዘጋጅ የስራ ቡድን ሰብሳቢ ወይም ለተቋሙ የሚቀርብ ማንኛውም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ በቃል ወይም በማናቸውም የጽሁፍ አይነት ሊቀርብ ይችላል።
2) በግልፅ የሚታወቅ ካልሆነ በቀር - የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ የጥያቄ አቅራቢውን አካል ማንነት፣ ፈቃድ/ህጋዊ እውቅና፣ አድራሻ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚገልፁ ማስረጃዎች ግልጽ ተደርገውና ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

## 10. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አደረጃጀት እና አሰጣጥ ሥርዓት

1) የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተቀላጠፈና የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅትን ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ ለመስጠት የሚያስችል የአደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት በባለሙያዎች የስራ ቡድኑ ውስጥ የሚፈጠር ይሆናል።
2) እንደአግባብነቱ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ አስፈላጊ ባለሙያ የሚመደብለት እና በእቅድ እና ሙያዊ ሥነ-ምግባር የሚመራ ስራ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል።
3) ለማናቸውም አካል በየትኛውም መንገድ የሚሰጥ መረጃ ለሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጁቱም ሆነ አጠቃላይ ለሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ውጤታማነት ወሳኝ ሚና የሚጫወት መሆኑ ተለይቶ ወቅቱንና ደረጃውን ጠብቆ ጥንቃቄ በተመላበት መልኩ ሊሰጥ ይገባል።

## 11. ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ የሚሰጥ ባለሙያ መመደብ ወይም መረጃ በተለያየ ቋንቋ እንዲሰራጭ ማድረግ

1) መረጃዎች በሀገር ውስጥ የመንግስት እና የግል የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት በተለያዩ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች (በዋናነትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በአፋርኛ እና በሶማሊኛ ቋንቋዎች) ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል።

2) በተለይም ባለሙያዎች የማይችሏቸው ቋንቋዎችን በተመለከተ - መረጃዎቹን - የቋንቋው ተናጋሪ ባለሙያ በመመደብ ወይም በሚዲያዎች በኩል ወደተለያዩ ቋንቋዎች እንዲተረጎሙ በማድረግ ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋሉ።

## 12. ለውጭ የመገናኛ ብዙሃን መረጃ የሚሰጥ ባለሙያ መመደብ

ለውጭ የመገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡ መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች (በዋናነትም በእንግሊዝኛ እና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች) መረጃ የሚሰጥ ባለሙያ ከስራ ቡድኑ ውስጥ ወይም በሌላ ዘዴ ይመደባል።

## 13. በማህበራዊ ሚዲያ መረጃ የሚያሰራጭ ባለሙያ መመደብ

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ቅድመ-ዝግጅት፣ የፖሊሲ ዝግጅት እና የድህረ-ፖሊሲ ዝግጅት ሥራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች በማህበራዊ ሚዲያ አውታሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ተደራሽ የሚያደርጉ ባለሙያዎችን ከስራ ቡድኑ ወይም በሌላ ዘዴ በመመደብ መረጃዎች ለዓለም ህዝብ እንዲደርሱ ይደረጋል።

## 14. የህዝብ አስተያየትና ሃሳብን የሚከታተል ባለሙያ መመደብ

1) በተለያዩ የመንግስት፣ የግል እና የውጭ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለህዝብ ይፋ በተደረጉ የሽግግር ፍትሕ ሂደቶችና ተግባራት ላይ የሚሰጡ የህዝብ አስተያየቶችን ተቋሙ ወይም የባለሙያዎች ቡድኑ ይከታተላል።

2) መሰረታዊ ማስተካከያ ሊያስከትሉ የሚችሉ አስተያየቶችን በማደራጀት ለሚመለከተው ከፍተኛ አመራር ወይም ለባለሙያዎች ቡድኑ የሚያቀርብ ባለሙያ እንዲመደብ በማድረግ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶች በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው እንዲካተቱ የሚደረግበት ሁኔታ ይመቻቻል።

## 15. የሚመለከተውን አካል ፈቃድ ስለማግኘት

1) ማንኛውም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሊታይ፣ ሊገመገም እና የሚመለከታቸውን አካላት ይሁንታ ሊያገኝ ይገባል።

2) በመሆኑም አስቀድሞ በተመለከተ የስራ አደረጃጀት እና ክፍፍል በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በቀር - ማንኛውም መረጃ ከመሰጠቱ በፊት የመረጃው መሰጠት አስፈላጊነትና ተገቢነት በሚመለከተው ከፍተኛ አመራር ወይም የባለሙያዎች ቡድኑ ሰብሳቢ እንዲታይና ይሁንታ እንዲሰጥበት ይደረጋል።

## 16. ትክክለኛ መረጃን ሙያዊ ሥነ-ምግባር በጠበቀ ሁኔታ መስጠት

1) ማናቸውም ከሽግግር ፍትሕ ጋር የተያያዘ መረጃ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊው ጥንቃቄና ቅድመ-ማጣራት ሊደረግበት ይገባል።

2) ከሽግግር ፍትሕ ጋር በተያያዘ የሚጋራ ማንኛውም መረጃ ትክክለኛነት ተረጋግጦና በፖሊሲ ዝግጅት ሥራው እንዲሁም በሀገርና ህዝብ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ታይቶ ካልተወሰነ በቀር እንዲሰጥ አይደረግም።

3) የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲሰጥ የተፈቀደለት ማንኛውም አካል የሚሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት የማጣራት እና የመረጃው ይዘት ከሂደቱ አላማ ጋር የማይቃረን፡ የፖሊሲ ዝግጅት ሥራውን የማያስተጓጉል፣ በህግ ያልተከለከለ፡ እና በሀገርና ህዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ጥቅም ላይ አሉታዊ ውጤት የማያስከትል ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሙያዊ ኃላፊነት አለበት።